*SOLUTIONS WITH DEBTERAW, VI*
*Call me by my name, address and title*
*By Obo Arada Shawl*

*March 13, 2009*

| |
|---|
| በዚሁ ዕለት በጥያቄ መልክ የቀረበው ጽሁፍ (colonialism-Ethiopianism-Democrasia) ለውውይይት ያመች ዘንድ በአማሪኛ ተተርጉሞ ቀርበዋል። |

ደወሉ ለማን ይቃጭል
ኢትዮጵያዊነት የማይጨበጥ ነው
ኤትዮጵያ-ኢዝም የሚጨበት ጉዳይ ነው
በሁለቱም ስምምነት ከሌለ
ምነው ዐግመላን የተባለ መድሀኒት ከደቡ (ደብተራው)እያለ

## ያላለቀው የደብተራው ጉዞ

ከ…
EPLF, TPLF እና OLF ጋር ሲነጻጸር

ለምን?
እንዴት? የደብተራው የሁሌ ጥያቄዎች ናቸው/ነበሩ

"በዛሬው ዕለት በሆዳዴው ጾም ሕዝቡ ይታሰራል"

## ለነፃ አውጪዎች የቅኝ ግዛት(colonialism) ትርጉም ምንድን ነበር?

የቅኝ አገዛዝ ከሕብረተሰብ ጋር አብሮ ያደገ ቢሆንም ቅሉ፣ ቋንቋው ግና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ገኖ በተለይም አውሮፓውያን "ስልጣኔን" ለኋላ ቀር ሕብርተሰቦች እንዲዳረስ ተብሎ የተዘረጋ ጽንሰ ሀሳብ ነው።ኢትዮጵያ "ያልሰለጠነች" ወደ ኋላ የቀርች አገር ነበርች ወይ? በአሁኑ ግዜስ ሻዕቢያ ወያኔ እና ኦነግ ስለዚሁ ጉዳይ ምን አቓም ይዘው ይሆን? ጣዕሳ-ፀፀት-Gaabuu- በስሜ ልጠራ፤ ስሜ ማነው? ቅኝ ገዢ ወይስ ተገዢ? መግለጫ (ገለጻ) ያስፈልገኛል!

በአንድ በኩል የቅኝ አገዛዝ ሰርዓት ከተገዢ አገሮች የሚሻው ነገር

- ንጥረ ነገሮች (Raw Materials)
- አዳዲስ ገበያ (Markets) እና
- አዲስ የመዋዕለ ንዋይ (Investments) መርበቦች ፍለጋ ናቸው

ኢትዮጵያ ጠጠኢ (mmi) ለማግኘት ስትል ኤርትራን ፣ትግራይን እና ኦሮሚያን ወርራለች ወይ? የሻዕቢያ፣የወያኔ እና የኦነግ መሪዎች ግለጹልን እባካችሁ?

በሌላ በኩል ደግሞ ቅኝ ገዢዎች ግዛት ለማስፋፋት ሲሉ ሠፋሪዎችን ከኢምፐሪያሊስት አገሮች ነቅሎ ወደ ለም መሬቶች ማስፈርን ይመለከታል። በአኤትዮጵያ ጉዳይ ማነው ኢምፐሪያሊስቱ? ተጨማሪ መግለጫ ይሰጠን! በኤትዮጵያ እኔ ከማውቀው በዕቅድ የተዘጋጀ የሰፈራ ፕሮግራም ወይም ግላዊና ተፈጥራዊ ዝውውር (ማይግረሽን) ታሪኩ የሚነግረን ከዚህ የተለየ ነው።

በተጨማሪም የቕኝ አገዛዝ ጉዳይ ሲነሳ በገዢዎችና በተግዢዎች ዘረኛነትና ባሕላዊ ሁነታዎችን

---

ባሕር-እምነት-ሥልጣኔ-መንግሥት-ተራራ (ባእሥመተ)

ይጨምራል ይህንንም እንደሚከተለው ይሆናል

- በፖለቲካ
- በሕጋዊ እና
- በምዝበራ

ኢትዮጵያ በአማራ ተመንዝራ የተገለጸችው በየትኛው የፖለቲካ፣ የሕግ እና የምዝበራ ቴዎሪ ነው ኤርትራን፣ትግራይንና ኦሮሚያን የቅኝ ግዛት ያደረገችው? የኤርትረያው ቀይ ባሕር፣ የትግራይ አሞሌ ጨው ወይስ የኦሮሚያ ቡና? በኤኮኖሚ እንዳልሆነ እንግባባ።

የቅኝ አገዛዝ ለተዛባ ልማት ቁልፍ ምክንያት ነው ይባላል፤የሻዕቢያ የወያኔ እና የኦነግ አመራሮች ስለ ልማት ያላቸው ግንዛቤ ምን ያክል ነው? ድንቁርና በዚህ ጉዳይ ላይ ምርቃን ይሆን? ልማት ሲሉ፣ ልማት ስንል አሁንም አልተግባባን!!!

በመጨረሻም ከሻዕቢያ ከወያኔ እና ከኦነግ አመራሮች አመለካከት ውጪ፣ የቅኝ አገዛዝ ጉዳይ በአይዶሎጂ ወይንም በሌላ እምነት ተጠቅሞ ብዝበዛን ወይንም ስርዓትን ለማንገስ ሲባል፣ ሕጋዊንትን ለማግኘት ጥረት ተደርገዋል፤ ሰለሆንም በተጨባጭ ሁኔታ ሲገመገም የኤትዮጵያ ቅኝ ገገሮች በተግባር የሻዕቢያና የወያኔ መንግስታት ሲሆኑ፣ ኦነግ ደግሞ በሃሳብ ደረጃ ተከትለዋል።

የቅኝ አገዛዝ በአብላጫው መሰረቱን ያደረገ በላቀ ሞራላዊና እሴታዊ ሆኖ ለተገገሮች የሚቸረቸር ጉዳይ ነው የተለየ ስሙም ዘረኝንት ወይም ሃሳዊ-ሳይንሳዊ ተብለዋል። የጎሰኝነትሰ ዓላማ ምን ይሆን ? ዘረኝነት ወይም ሌላ? ለሁሉም ኤትዮጵያዊ/ት ዕንቆቅልሽ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡

## ማንን ኢትዮጵያዊ/ት?

- በጆግራፊያዊ ክልል ኢትዮጵያ (MAKK)/ኤትዮጵያ ክልል ውስጥ የተወለዱ (by Birth)
- በኤወይ አብዮት የተታገሉት ሁሉ ወይም በመታገል ላይ ያሉ (by Naturalization)
- ኤትዮጵያውያንን ያገቡ (by Marriage)
- በኤትዮጵያውያን ጉደፈቻዎች ሆነው ያስመሰከሩ (Adoption) እና
- ሌሎችም በሌላ ምክንያት ዜግነት ሊያማሉ የሚችሉ ነገር ግን ከላይ ያልተጠቀሱ (such as Diaspora)

ሁሉ በተጨባጭ በ"ኢዝም" ዜጋዎች ይሆናሉ!!! በልበ-ሙሉ ኢትዮጵያዊ/ት ነኝ ብለው ሊምሉ ሐበሽ፣ትግሪ፣ኦርሞ ወዘተ ላይሉ።

## ዴሞክራሲያ እንዴት?

በባህላችን በዓይን አይቶ ፍርድ፣ መፍረድና መፈረድ ያለና የነበረ ጉዳይ ነው። የፍርድ፣ በፈራጆች፣ ለፈራጆች እየተባለ ለዘመናት የተነገረና የተደረገ በአሁኑ ዘመን አጠራር ደግሞ ዴሞክራሲ ተብሎ፣ ትርጋሜው አስተዳደር የሕዝብ፣ በሕዝብ፣ ለሕዝብ ለሚለው ገላጭ ነው። እኛ የሚለው ቃል በባሕላችን የዘለቀ ስለሆነ በዚሁ መጠን ሌሎችን የምንፈርደው በእኛነት መለኪያ መሆኑን ነው።ኤትዮጵያውያን በበጎ ሥነ ምግባር የምንቀሳቅስ እንጂ በጽሁፍ እገዳ (edict) ወይም በድምጽ ብልጫ (vote) የምንቀሳቀስ አልነበርንም/አይደለንምም።

የሚገርመው ነገር የፕረዚደንት ኬነዲ ንግግር “መጠየቅ ያለብህ/ሽ አገርህ የምታደርግልህ ሳይሆን አንተ/ቺ ለአገርህ ምን ታደርግላት አለህ/ሽ” የሚለው ጥቅስ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የብዙ አድርባዮች ልብ ነክቶዋል። ለተራማጅ የተማሪዎች ንቅናቄ ድርጅት (እንደነ ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ አፃፃፍ ሳይሆን) ለአገራቸው መስዋእት ለመሆን የተዘጋጁ ብፁኣን ነበሩ። የፕረዚደንት ኬነዲ ጥሪ ኣላስፈለጋቸውም ነበር።

**ዴሞክራሲያ** - የኢሕአፓ የፖለቲካ ልሣን እንደመሆኑ መጠን በዚህ በየካቲት ወር ሁለት እትሞችን 34ኛው እና 35ኛው ታትሞ ወጥተዋል። የመጀመሪያው እትም ለኤትዮጵያ ወጣቶች ጥሪ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የካቲትን አስመልክቶ “የካቲት ግም ሲል” ይለዋል።

*<u>“የዴሞክራሲያ ጥያቄና ትግል በኤትዮጵያ”</u>* ለቅኝ አገዛዝ አባዜ፣ ላልተጨበጠ ኢትዮጵያዊነት ፋከራ(እንደነ ኢትዮጵያ ትቅደም)፣ ለአምባ ገነኖች ዱላ፣ ለዋሾች ቱልቱላ ፍቱን መድሃኒት መሆኑን ኢሕአፓ ከተገነዘበና ከታገለ ሁለት ትውልድ አልፈዋል። ሰሚ ጆሮ ግን አጣ።

## የደብተራው ጥሪ በተግባር

- የአሜሪካና እስራኤል ፍላጎት በኤትዮጵያ ምንድን ነው? እንወቀው!
- የሩሲያና የቻይና ጥቅምስ በምን ላይ የተመሰረተ ነው? እንወቀው!
- የአውሮፓውያን የጋራ ፍላጎትስ ምን ይመስላል? እንወቀው!
- የአረቦችና የእስላም አገሮችስ ለምን ጨዋታው ውስጥ ይገባሉ? እንወቀው!
- ሻዕቢያና ወያኔ በእንዴት ሁኔታ ሥልጣን ለሕዝብ ያስረክባሉ? እንወቀው!

ጠንቅቀን እንወቀው። “ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እንዳይሆን” አምስቱ ጥያቄዎችን በአንድነት ቢመለሱ መልካም ነው።

ለግንዛቤ እንዲረዳ ወይም እስትራተጂ እንዲቀየስ ከዚህ በታች ያለውን ይመልከቱ፡

1. የሻዕቢያው መሪ ፀረ-ዴሞክራሲያ ብቻ ሳይሆን በዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ ፈጽሞ አያምንበትም፡፡ ለምን ብሎ መጠየቅ? እስከመቸ በማይከሸሊያን አመራር?
2. የወያኔው መሪ አጼያዊ አስተሳሰብ ስለአለው በስመ ዴሞክራሲያ እያታለለ ሥልጣኑን ለማራዘም መጣሩ ይቀጥላል። እስከመቸ መታለል?
3. ካልሆነም፣ ፀረ-ዴሞክራሲያ ወይንም አጼያዊ አስተሳሰብ ከሌላቸው እስቲ ስለ ደብተራው ጉዳይ ይንገሩን ምክንያቱም ዴሞክራሲያና ደብተራው አይነጣጠሉምና ነው።

የሻዕቢያው ድርጅት ለፍትሕና ለዲሞክራሲያ ነው የምታገለው ብሎ በግልጽ ጽፈዋል የወያኔው ድርጅት መሪ ደብተራው አስተማሪያችን፣ ዋለልኝ አንጎላችን፣ መለስ ተክሌ ስማችን ብሎ ከሚለፈልፍ ስለ “ዴሞክራሲያዎች” ሀቁን ለምን ደበቀው?

እንግዲያውስ “ፍትሕ ለምን የለም? የዴሞክራሲያ ጥያቄ የት ደረሰ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። ለሁለቱም መሪዎች መፈተኛቸው ያው የምሁሩና የአገር ወዳዱ ጀግናው “የደብተራው፣ፀገየ ገብረመድህን ጉዳይ መሆኑ እንገንዘብ።”

ፍትሕና ዴሞክራሲያ የት አሉ ብለን መጠየቅ ካልቻልን
ሁሉም በፀሎት ከሆነ መልሱ … እንጠብቃለን <u>*ፋሲካ*</u> እስቲፈታ:

**እውነት ታቸንፋለች!**

woldetewolde@yahoo.com

ለማሳሰብ

በወርሃ የካቲት ብዙ ተጋድሎች፣ብዙ የኑሮ ምስቅልቅሎች ተደርገዋል። ከ1966 ዓም ጀምሮ በኤትዮጵያ ጦርነቶች፣ አብዮቶች፣ ግድያዎች፣ዕብደቶች፣ ምንዝርናዎች፣ ሙስናዎች፣ የሃይማኖት እምነቶች መቀየር፣የመሳሰሉት እና የግድያ ሙከራዎች ተደርገዋል። ነገር ግና የሥልጣን ማስረከብ (power abdication) አልተደረገም/አልታየምም። ለምን ይሆን? Why and How? READ, READ,and READ !!!